# ስለፉትስክሬይ የማህበረሰብ ኪነጥበባት ማዕከል

ፉትስክሬይ የማህበረስብ ኪነጥበባት (ፍትስክሬይ ኪነጥበባት) በማህበረሰቦች ላይ የሚያተኩር የኪነጥበባት እንቅስቃሴዎችን ወይም ተሳትፎዎችን ለማቀናበርና ለማዘጋጀት ከማህበረሰቦችና ከኪነጥበብ ሰዎችጋር ይሰራል፡፡ ይህ እንቅስቃሴም የሚከተሉትን ያካትታል፡

- የኪነጥበባት ፕሮዤዎችን ማዳበር
- ፕሮግራሞችን፣ ወርክሾፖችን፣ እና ትዕይንቶችን ማቅረብ
- በግለሰቦች፣ በቡድኖች፣ እና በድርጅቶች የሚደረጉ ማህበረሰባዊ ትኩረት ያላቸው የኪነጥበብ የእድገት እንቅስቅቃሴ ጥረቶችን መደገፍና ማበረታታት
- በማዕከሉ ያሉንን ቦታዎች ለወርክሾፖች፣ ለጉባዔዎች፣ ለበዓላት፣ እና ለሌሎች ትዕይንቶችም በመገናኛ ቦታነት እንዲገለገሉባቸው ማከራየት

የፉትስክሬይ ኪነጥበባት የሚገኘው በሄንደርሰን ቤት ውስጥ ሲሆን መጋዘኑም በማሪባይርኖንግ ወንዝ ዳርቻ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ወንዝ አውስትራሊያ ውስጥ የሜልበርን ምዕራባዊ  ክልልን ይዞ ይወርዳል፡፡ የኩሊን ብሄር በሆነው በውሩንጀሪ ጎሳ ባህላዊ መሬት ላይ የምንገኝ መሆናችንን እናረጋግጣለን፡፡ በነዚህ ባህላዊ መሬቶች ላይ የሚኖሩ የሀገሬው ሽማግሌዎችን እናከብራለን፣ በነሱም በኩል ለአቦሪጂናልና ለቶሬስ ስትሬይት ደሴቶች ኗሪ ህዝቦች ሁሉ አክብሮታችን እንዲደርስ እናደርጋለን፡፡

ፉትስክሬይ ኪነጥበባት ከ1974 (1967/68) ዓ.ም ጀምሮ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ድርጅቱ፣ የማህበረሰብ ኪነሬጥበባትን በመደገፍና በማበረታታት እንዲሁም በአውስትራሊያ ውስጥ የህብረ-ባህላዊ ኪነጥበባትን በማዳበሩ ስራ ላይ ቀዳሚነትን በመውሰዱ እጅግ በጣም ሰፊ ብሄራዊ እውቅናን አግኝቷል፡፡ በኪነጥበብና በማህበረሰብ መካከል ያለው ስብጥራዊና ትስስራዊ ኃይል ስናጤን እንድንነሳሳ ተገፋፋን፣ ከዚህም ተማርን፣ በውጤቱም የመፍጠር፣ የማሰብና ማሰላሰል፣ የመጠቀምና የመተባበር አዲስ መንገዶችን አውጠነጠንን፡፡

# ምን እንደምሰራ

ስራችን የሚከተሉትን ክፍሎች ያካትታል፡

- **ፕሮዤዎች፡** ኪነጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን ተፎካካሪ ሚና በሚመለከት ማህበረሰባዊ የኪነጥበባት ፕሮዤዎችን እናዘጋጃለን፡፡ ፕሮጀክታችንም ከበርካታ የተለያዩ ግለሰቦች፣ ማህበረሰቦች፣ የኪነጥበብ ማህበራትና ከትድርጅቶች ጋር ይሰራል፡፡
- **ፕሮግራሞች፡** ፕሮግራሞቻችን የሚከተሉትን ያካትታሉ፡ በሁሉም የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎችን የሚያሳትፍ የወርክሾፕ ፕሮግራም፣ የኪነጥበብ ባለሙያ ፕሮግራም፣ የኪነጥበብ ህይዎት፣ (ማለትም አካለ ጎደሎዎች በኪነጥበብ ስራ እንዲሳተፉና የኑሮ ዘደን እንዲያዳብሩ የሚረዳ ፕሮግራም)፣ እና ኢንኩቤተርስ (ከፉትስክሬይ ኪነጥበባት ጋር ቁርኝት ያላቸውን የተለያዩ ቡድኖችን እድገት የሚያግዝ ፕሮግራም)
- **ትዕይንቶች፡** የትዕይንቶች ፕሮግራማችን የትዕይንት (የድርጊት) እንቅስቃሴዎችን፣ ፎረሞችን፣ በመዳበር ላይ ያለ ኪነጥበብ ማሳዬትን፣ ስለኪነጥበብ መነጋግርን፣ እና የኪነጥበባት ውጤቶችን ማሳየትን (ኤግዚቢሺን) ያካትታል፡፡

# ያግኙን

ተጨማሪ ማብራሪያዎችን የሚሹ ከሆነ በሚከተሉት አድራሻዎቻችን ያግኙን፡

Footscray Community Arts Centre
45 Moreland Street
Footscray
Victoria, Australia 3011

+61 3 9362 8888 (ስልክ)
+61 3 9362 8866 (ፋክስ)

reception@footscrayarts.com

www.footscrayarts.com

የሚፈልጉ ከሆነ፣ ነጻ የስልክ አስተርጓሚ አገልግሎት ልናዘጋጅ እንችላለን፡፡